# አንበሶችን ከጥፋት ለመታደግ የወጣ ይፋዊ መግለጫ



የአንበሶች ህልውና በቀውስ ላይ መሆኑን ሁላችንም የምንስማማበት ጉዳይ ነው፤ ባለፉት 25 አመታት ብቻ ቁጥራቸው በግማሽ አሽቆልቁሏል። በአሁኑ ጊዜም በአፍሪካ ከ20,000 የማይበልጡ አንበሶች በዱር ውስጥ እንደቀሩ ይገመታል። በተጠናከረ የጋራ ጥረት አንበሳና የተፈጥሮ መኖሪያ አካባቢው ያላቸውን ህልውናዊ ቁርኝት ወደነበረበት ደረጃ መመለስ እንችላለን።



የአፍሪካ ሀገራት መሪዎችና በአንበሶች መዳረሻ ስፍራዎች የሚኖሩ ማኅበረሰቦች ለአንበሳ ዝርያ ህልውና ቀዳሚ ባለቤቶች ናቸው።

አንበሳ የኢትዮጵያዊያን ባህላዊና ማኅበራዊ ውክልና የዓለም ቅርስ መሆኑን እንገነዘባለን።

የአንበሳ ዝርያ ህልውና መሻሻል እንደሚችል እናውቃለን።



ስለዚህም፤

## ጥፋቱን እናስቁም

አንበሳ የሚመገባቸውን የዱር እንስሳትንና የመኖሪያ አካባቢያቸውን እንጠብቅ።

## ጫናውን እንቀንስ

በአንበሶች መዳረሻ አካባቢ የሚኖሩ ማኅበረሰብ የኑሮ ጫና እንቀንስ።

## ፋይዳውን እናጉላ

አንበሶች ለሀገር ብሎም ለዓለም ያላቸውን ባህላዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ እና ሥነ ምህዳራዊ ፋይዳ በማጉላት ያለውን የዕውቀት ክፍተት እንሙላ።